Amharic | አማርኛ

ፌብርዋሪ 2026

homes victoria

BIG HOUSING BUILD

# የFlemington

ማህበረሰብ ዝመና



**በቦታው ላይ ምን እየሆነ ነው**

### ቅድሚያ የሚሰጠው የአየር ማቀዝቀዣ ተከላ

ስራዎች ይቀጥላሉ

### በ29 ክራውን ስትሪት፣ የሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች መልሶ የማልማት ሥራ የሚቀጥለው ደረጃ

በሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን እና ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን የሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች መልሶ የማልማት ሥራ በሂደት ላይ ነው።

### በኒው ሆላንድ ኮርት ልማት ሥራዎች ወደ ውስጥ እየተሻገሩ ነው

በአዳዲስ አፓርታማዎች ውስጥ ሥራ ሲጀምር ድምጽ መቀነሱ ማስተዋል ሊጀምሩ ይችላሉ

# በሆላንድ ኮርት የመጀመሪያው አፓርታማ ተጠናቅቋል

አዲስ ባህሪያት ለማየት የQR ኮድን ስካን ያድርጉ

ቤቶች ቪክቶሪያ የአቦርጂናል እና የቶረስ ስትሬት ደሴት ነዋሪዎችን የምድሪቱ ባህላዊ ጠባቂዎች አድርገው ይቀበላሉ እና ያለፉትን እና የአሁኑን ሽማግሌዎቻቸውን እውቅና ሰጥተዋል እና ያከብራሉ።

## 29 ክራውን ስትሪት፣ የሰማይ ጠቀስ ፎቅ መልሶ ማልማት ቀጣይ ደረጃ አካል ነው

ነዋሪዎች አሁን ምንም ነገር ማድረግ አያስፈልጋቸውም።

ከ2026 አጋማሽ እስከ ፌብሩዋሪ 2028 ድረስ፣ በአቅራቢያ ያሉ ቤቶችን ጨምሮ ፍላጎቶችዎን የሚያሟላ ቤት ለማግኘት ከነዋሪዎች ጋር በቅርበት እንሰራለን።



በዚህ አመት መጨረሻ ላይ በ29 ክራውን ስትሪት ላይ ያሉ ነዋሪዎችን በሆላንድ ኮርት፣ ፍሌሚንግተን የተጠናቀቁትን አፓርታማዎች ውስጣቸውን እንዲያዩ እንጋብዛለን።

| ቀን | ደረጃ |
| --- | --- |
| January/ጥር 2026 | እዚህ ያለነው ጥያቄዎቻቹ ለመመለስ ነው። |
| ፌብርዋሪ 2026 | የማህበረሰቡን ፍላጎቶች ለመረዳት እርስዎን ማዳመጥ። |
| ማርች 2026 – አፕሪል 2026 – ሜይ 2026 | **ቀጣይነት ያለው የማህበረሰብ ተሳትፎ** |
| ጁን 2026 | የማዛወር ድጋፍ እና የማዛወር ማዕከሎች ክፍት ናቸው። |
| ጁላይ 2026 – ፌብርዋሪ 2028 | **ተከራዮች ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር ይደገፋሉ** |

## የመረጃ ዝግጅቶች ለነዋሪዎች፣ ጓደኞች እና ቤተሰብ

በ29 ክራውን ስትሪት ላይ ካሉ ነዋሪዎች፣ እንዲሁም ከጓደኞቻቸው እና ቤተሰባቸው ጋር በአካል እና በበይነ መረብ ለማነጋገር እዚህ እንገኛለን። ለዝግጅት ቀናት እና ሰዓቶች የፎየር ፖስተሮችን ይመልከቱ ወይም **homes.vic.gov.au/events** ይጎብኙ።



## እንደተገናኙ መቆየት

**ተሳታፊ ለመሆን ከታች ያለውን ይጎብኙ፦**

**የምክክር አስተያየት**

**ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት መመዝገብ**

ተሳታፊ ሆኖ ለመቆየት ከታች ያለውን ይጎብኙ፦

homes.vic.gov.au/flemington-precinct

በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ **Homes Victoria** ብለው በመፈለግ ይከተሉን።



በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place፣ Melbourne።
© የቪክቶሪያ ግዛት፣ ሆምስ ቪክቶሪያ፣ ፌብሩዋሪ 2026። (HV002626)።
በFinsbury Green, Melbourne Victoria, 3000 የታተመ።

More Homes For Victorians

VICTORIA State Government

# ፌብሩዋሪ 2026፣
## በፍሌሚንግተንምን እየተካሄደ ነው



### ሆላንድ ኮርት
286 አዳዲስ ቤቶች እና የህዝብ መናፈሻ

**ስራ በሂደት ላይ ነው**

- የግንባታ መዋቅር አሁን ተጠናቅቋል ሰለሆነም የማማ ክሬኖች ተነስተዋል
- በአፓርታማዎች ውስጥ ሥራ እየተጀመረ ነው
- ለመጀመሪያዎቹ አፓርታማዎች የጥራት ማረጋገጫ በመካሄድ ላይ ነው
- በሕዝብ መናፈሻ ላይ ስራዎች እየተጀመሩ ነው

### 12 ሆላንድ ኮርት (Holland Court)

**ህንጻዎችን መጠበቅ**

- ክፍት አፓርታማዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ ማድረግ
- ክፍት ባዶ በሆኑ አፓርታማዎች፣ ኮሪደሮች እና የኤለቨተር ቦታዎች እና ከህንጻው ውጭ በተሰዩ ቦታዎች ላይ ትናንሽ የቁሳቁስ ናሙናዎችን መውሰድ
- ቁም ሣጥኖችን፣ የወለል ንጣፎችን እና ሌሎች ትናንሽ እቃዎችን ከባዶ አፓርታማዎች ለማስወገድ ስንዘጋጅ በሆላንድ ኮርት እና አካባቢው አንዳንድ ለውጦችን ያስተውላሉ
- ለሠራተኞች ጊዜያዊ መገልገያዎች ይዘጋጃሉ
- የቆሻሻ መጣያዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማስወገድ ቦታ ለመፍጠር አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የመኪና ማቆሚያዎች ይታጠራሉ
- ይህንን የመኪና ማቆሚያ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ እባክዎን መኪኖች መቼ መነሳት እንዳለባቸው ለማረጋገጥ ማሳወቂያዎችን ያከታተሉ




### 126 እና 130 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)

**የኤሌክትሪክ ስራዎች**

- የኤሌክትሪክ ስራዎች የተሻሻሉ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶችን መደገፋቸውን ቀጥለዋል

**ቅድሚያ የሚሰጠው የአየር ኮንዲሽነር ተከላ በ126 ሬስኮርስ ሮድ ቀጥሏል**

### ጥቃቅን የመንገድ ስራዎች

- በሆላንድ ኮርት ላይ በጠርዝ እና በእግረኛ መንገድ ላይ የተደረጉ ለውጦች
- የእግረኛ መንገድ ለአጭር ጊዜ ይዘጋል
- ተሽከርካሪዎችን እና እግረኞችን ለመምራት የትራፊክ አስተዳደር ይደረጋል

### 120 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)

**ህንጻዎችን መጠበቅ**

- ክፍት አፓርታማዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ ማድረግ
- ክፍት ባዶ በሆኑ አፓርታማዎች፣ ኮሪደሮች እና የኤለቨተር ቦታዎች እና ከህንጻው ውጭ በተሰዩ ቦታዎች ላይ ትናንሽ የቁሳቁስ ናሙናዎችን መውሰድ

ስራችን የሚመራው በምክር ቤትዎ መደበኛ የስራ ሰዓታት ነው -

| ከሰኞ እስከ አርብ | ቅዳሜ |
|---|---|
| ከ7am እስከ 6pm | ከ9am እስከ 3pm |

ተጨማሪ መረጃ ለሚፈልጉ ነዋሪዎች የአካባቢዎን የመኖሪያ ቤቶች ቢሮን ያነጋግሩ፡-

1300 360 462　ascotvale.housing@dffh.vic.gov.au

አንዳንድ ጊዜ ከእነዚህ ሰዓታት ውጭ ለመስራት የምክር ቤት ፈቃድ ያስፈልጋል ነገርግን ይህ ከተከሰተ ነዋሪዎችን እናሳውቃለን።

ሁሉም ስራዎች በከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎች እና ህጋዊ መስፈርቶች ይከናወናሉ።

## የመልሶ ማልማት ስራዎች የጊዜ ሰሌዳ

12 ሆላንድ ኮርት (Holland Court) እና 120 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)

**ነዋሪዎች በእነዚህ ሕንፃዎች ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ምንም ዓይነት ማፍረስ አይደረግም።**

2025

### 1. የበለጠ መማር እና ነገሮችን ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ

- ክፍት ባዶ አፓርታማዎችን ደህንነታቸው የተጠበቀ ማድረግ
- ቁሳቁሶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስተዳደር ጣቢያውን እና ህንጻዎችን መመርመር
- መደበኛ ጥገናን መቀጠል

**2026፡- እዚህ ነን**

### 2. ዝግጁ መሆን

- ለደህንነት ሲባል ጣቢያ እና ምልክት ማዋቀር
- የአገልግሎት ግንኙነቶችን መፈተሽ
- ለእግረኞች፣ ለመኪናዎች እና ለመኪና ማቆሚያ ጥቅም በሚውልበት ወቅት ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ
- ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በህንፃዎች ውስጥ እየሰራን ነው
- ቁም ሣጥኖችን፣ የወለል ንጣፎችን እና ሌሎች ትናንሽ እቃዎችን ከባዶ አፓርታማዎች ማስወገድ

### 3. ፈረሳ

- ስካፎልዲንግ/ መወጣጫ መትከል
- ጥንቃቄ በተሞላበት ደረጃዎች ግንባታን ማፍረስ
- መደበኛ የማህበረሰብ መረጃዎች

በቋንቋዎ ውስጥ መረጃን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ይጎብኙ - **homes.vic.gov.au/information-in-your-language**

ለአጠቃላይ ጥያቄዎች የኢሜይል ኣድራሻ:

**enquiries@homes.vic.gov.au**